# ለአንድ ሳምንት ሲካሄድ የቆየው የዳርት ሻምፒዮና ተጠናቀቀ

ግርማ መንግስቱ 05-20-17
(girmaexplore@gmail.com)

በኢትዮጵያ ዳርት ፌደሬሽን አዘጋጅነት ከግንቦት 5 2009 አ/ም ጀምሮ በአዲስ አበባ፣ በ"የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት ማእከል" ዘመናዊ ጂምናዚየም ውስጥ፣ በክልሎች እና ከተማ መስተዳድሮች ተሳታፊነት ሲካሄድ የሰነበተው አገር አቀፍ የዳርት ሻምፒዮና ባለፈው ቅዳሜ ተጠናቀቀ። በአዘጋጆቹ እንደተገለፀው፣ ውድድሩ እጅግ ፉክክር የታየበት፣ ፍፁም ወንድማማችነት የሰፈነበትና ስፖርታዊ ጨዋነትና ወዳጅነት የነገሰበት ሆኖ አልፏል። ወደ ውድድሩና አጠቃላይ ውጤቱ ከመሄዳችን በፊት ስለዳርት ስፖርትና ስፖርቱን በባለቤትነት ስለሚመራው *የኢትዮጵያ ዳርት ፌደሬሽን* በማንሳት ጥቂት እንበል።

መነሸው ጥንታዊ የግሪክ ወታደራዊ ተቋማት መሆኑ የሚነገርለት ዳርት ስፖርት በሀገራችን ተወዳጅ ከሆኑትና ለረጅም ጊዜያት በመከናወን/መዘውተር ላይ ከሚገኙት የስፖርት አይነቶች መካከል አንዱ ሲሆን፤ ስፖርቱ የዕድሜ፣ ፆታ፣ ሀይማኖት፣ ዘርና ቀለም ልዩነት ሣይገድበው ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር አካሉንና አዕምሮውን ለማዳበር፤ ጤናውን ለመጠበቅ፣ በመስኩም ተወዳዳሪ ለመሆን የሚሳተፍበት የስፖርት አይነት ነው፡፡

ዳርት ስፖርት ከቤት ውስጥ ጨዋታዎች መካከል አንዱ (ባለሞያዎች "indoor game of accuracy in which players tosses small, arrowlike, weighted missiles" ሲሉ ይገልፁታል) ሲሆን በጣም ተወዳጅ፣ ተዝወታሪና በትንሽ ቦታ ላይ የሚከናወን ስፖርት መሆኑም ከሌሎቹ የስፖርት አይነቶች ለየት ሲያደርገው፤ አካልን ብቻ ሳይሆን አእምሮንም የሚያነቃቃ፣ ከፍተኛ የማሰብ ችሎታን፣ በጥንቃቄ ማለምና ማነጣጠርን የሚጠይቅ፣ አዝናኝና አስደሳች ስፖርት መሆኑም ልዩ መገለጫው ነው።

ይሁን እንጂ፣ ስፖርቱ በሀገራችን ከተጀመረ (እንደሌሎቹም ባይሆን) አመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም በሚፈለገው ደረጃ፣ በሁሉም ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች እየተዘወተረ ነው ማለት ግን አይቻልም። ለዚህ ደግሞ እንደሌሎች የስፖርት አይነቶች ልዩ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑ እና የማዝወተሪያም ሆነ መወዳደሪያ ስፍራ አለመኖሩ በዋና ምክንያትነት ተጠቃሽ ናቸው።

ዳርት ስፖርት በተለያዩ አገራት ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኘ፤ በከፍተኛ ደረጃም በመዝወትር ላይ የሚገኝ የስፖርት አይነት ነው። በምሳሌነት ከሚጠቀሱ አገራት መካከልም እንግሊዝ የምትገኝ ሲሆን፤ ይህም "The game is one of the most popular in taverns and clubs in Britain." ተብሎ በጥናቶች ላይ ተገልፆ ይገኛል። (በዚህና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የበለጠ ግንዛቤን ለመያዘ የአለም አቀፍ ዳርት ፌደሬሽን (WDF)ን ኦፊሴላዊ ድረ-ገፅ መመልከት ተገቢ ይሆናል።)

ይህ የስፖርት አይነት በሀገራችን እውቅና የተሰጠው ሲሆን፤ የሚመራውም በአዋጅ በተቋቋመና ራሱን በቻለ ተቋም ነው። ተቋሙም "የኢትዮጵያ ዳርት ፌዴሬሽን" ሲሆን፤ በመላ አገሪቱ የዳርት ስፖርትን ለማሳደግና ለማስፋፋት የተቋቋመ፤ ከህዝብ በተመረጡ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሰጪ አባላት በተዋቀረ ስራ አፈፃሚ የሚመራና በፌደራል ስፖርት ኮሚሽን በሚደረግለት የፋይናንስና ባለሙያ ድጋፍ የሚንቀሳቀስ የዳርት ስፖርት ማህበር ነው።

*በዳርት ስፖርት ምርጥ፣ ብቁና አስተማማኝ የሆኑ ተጨዋቾችን ማፍራትና ስፖርቱ በህብረተሰቡ ዘንድ ተወደጅና ተዘውታሪ እንዲሆን በማድረግ የስፖርቱን ተደራሽነትና የእድገት ደረጃ ከፍ ማድረግ፤ ከአገር አቀፍ እስከ ታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ድረስ ህዝባዊ መሰረት ይዘው በየደረጃው በተቋቋሙ ፌዴሬሽኖች/ማህበራት/ክበባት እንዲደራጁና በህግና ደንብ እንዲመሩ፤ ግልፅ፣ ተጠያቂነት ባለበትና አሳታፊ የሆነ የአሰራር ስርአትን በመዘረጋት ዜጎች እንደየ እድሜያቸው፣ ፆታቸው፣ ፍላጎትና ዘንባሌያቸው በዳርት ስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤*

አቢይ አላማው፤

*በሀገር አቀፍ ደረጃ፣ በዘጠኝ ክልሎች እና በሁለት ከተማ መስተዳድሮች መካከል የእርስ በርስ ግንኙነትን በማጠናከር ስፖርታዊ ወዳጅነትን መፍጠር፣ በአመታዊ ውድድሮች አማካይነት አገርን የሚያስጠሩ ምርጥ የብሔራዊ ቡድን ስፖርተኞችን ማፍራት፤*

ግቡ የሆነው የኢትዮጵያ ዳርት ፌዴሬሽን ሰባት አባላት ባሉት ስራ አስፈፃሚ የሚመራ፣ የፅ/ቤት ሀላፊና ባለሞያዎች ያሉት ማህበር ሲሆን፤ በዚሁ አቢይ አላማውና ግቡ መሰረትም፣ ስፖርቱ በሁሉም የአገራችን ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች እንዲስፋፋና ተዝወታሪ እንዲሆን ለማድረግ፤ ፌደሬሽኑ አቅም በፈቀደ መጠን አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ በማድረግ ላይ ይገኛል።

ይህ ብቻ አይደለም፣ ፌደሬሽኑ ከተለያዩ ድጋፍ ሰጪና ከስፖርቱ ተቆርቋሪ ግለሰቦች፣ ተቋማት፣ ድርጅቶች ወዘተ ጋር በመተባበር በሁሉም ተቋማት (ት/ቤቶች፣ መስሪያ ቤቶች፣

ወጣት ማእከላት፣ መዝናኛ ስፍራዎች፣ ሆቴሎች ወዘተ) የዳርት ስፖርትን የማስተዋወቅ፣ ማስፋፋትና ውድድሮችን የማካሄድ ስራን እየሰራ ይገኛል።

የፌዴሬሽኑ ፕሬዘዳንት አቶ ተስፋዬ ጎይቴ የዘንድሮውን አገር አቀፍ ሻምፒዮና አስመልክተው እንደገለፁት በሌላው አለም ሰፊ ተሳትፎና ተቀባይነት ያለው ዳርት ስፖርት በሀገራችንም እንዲስፋፋ፣ ህዝባዊ መሠረት እንዲኖረው፣ ተዝወታሪ እንዲሆን ከማደረግና አገራችን ለተያያዘችው ፈጣን እድገትና ገፅታ ግንባታ ተግባር የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ፤ ህብረተሰቡን የዘርፉ ተጠቃሚ ለማድረግና በሀገራችን ስፖርታዊ ወዳጅነትን ማጠናከር ይቻል ዘንድ፤ ከክልል ፌደሬሽኖችና ማህበራት ጋር በመሆን ከታች፣ ከቀበሌ ጀምሮ መርሀ ግብር ተዘጋጅቶለት በመሰራት ላይ ነው። ይሁን እንጂ፣ ይህ የፌደሬሽኑ እቅድ የበለጠ ይሳካ ዘንድ የበርካታ ባለድርሻ አካላትን የሙያና ፋይናንስ እገዛ ይፈልጋል።

የፌደሬሽኑ ፅ/ቤት ሀላፊ አቶ ጥላሁን አላምረው በመላ ሀገሪቱ ዳርት ስፖርትን ለማስፋፋትና ለማሳደግ ከፍተኛ ሀላፊነት የተሰጠው የኢትዮጵያ ዳርት ፌደሬሽን ስፖርቱ ሰፊ ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው ለማድረግና ከዘርፉ አገርና ህዝብ ሊያገኙ የሚገባውን ማንኛውንም ጥቅም አሁን ካለበት ወደ ላቀ ደረጃ ከማሸጋገር አኳያ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ሁለንተናዊ ተሳትፎና ትብብር የሚጠይቅ፣ በተለይም የህዝቡን ተጠቃሚነትና ዘርፉን ከማልማት አንፃር በመንግስት በኩል ልዩ ትኩረትና ድጋፍ የተሰጠው መሆኑንና በፌደሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ በኩልም የረጅም፣ መካከለኛና አጭር ጊዜ እቅድ ተይዞ ሰፊና አገር አቀፍ እንቅስቃሴ እየተደረገ እንደሚገኝ፣ በአተገባበሩ ላይም የክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ተሳትፎ ከፍተኛ መሆኑን ገልፀዋል።

እንደአቶ ጥላሁን ማብራሪያ አገር አቀፉ ፌደሬሽን ለክልሎች፣ ከተማ መስተዳድሮችና ሌሎች እገዛ ፈላጊ ክለቦች የሚሰጣቸው በርካታ አገልግሎቶች አሉ፤ ከአገልግሎቶቹ መካከልም ህብረተሰቡ በሚኖርባቸውና በሚዝናናባቸው ስፍራዎች ሁሉ ዳርት ስፖርትን በማስፋፋት ህብረተሰቡን ተሳታፊና ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል አደረጃጀትን ከቀበሌ እስከ አገር አቀፍ ድረስ መዘርጋትና ማጠናከር፣ የማሰልጠኛ ማኑዋሎችን በማዘጋጀት ማሰራጨት፣ ስልጠናዎችን መስጠት፣ መርሀ ግብር በማዘጋጀት አገር አቀፍ ውድድሮችን ማካሄድ፣ በአለም አቀፍ ውድድሮች ላይ አገርን ወክለው የሚሳተፉ ጠንካራ ፕሮፌሽናሎችን ማፍራት፣ የስፖርቱ አጋርና ደጋፊ አካላትን ማሰባሰብና የመሳሰሉት ዋና

ዋናዎቹ ናቸው። በዚሁ መሰረትም ላለፉት በርካታ አመታት በሀገር አቀፍ ደረጃ፣ ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች የተሳተፉበት አመታዊ የዳርት ሻምፒዮና ውድድሮች ሲካሄዱ ቆይተዋል፤ በሂደቱም ስፖርቱን ከማስተዋወቅ፣ ተወዳጅና ተዝወታሪ ከማድረግ ባሻገር በዘርፉ ታዋቂ ስፖርተኞችን ለማፍራት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ሲሆን፣ አበረታች ውጤትም በመገኘት ላይ ነው።

በየክልሉ የሚገኙ ስፖርተኞችን በጋራ በማገናኘት ምርጥ ተሞክሮዎችን የሚቀስሙበት፣ የራሳቸውንም ለሌላው የሚያካፈሉበት፣ የተሻሉ ልምዶችን የሚለዋወጡበት፣ ወጣቶች በውድድሩ ተሣታፊ በመሆን የእርስ በእርስ ትውውቅ የሚያደርጉበትና ያላቸውን መልካም ግንኙነትን የሚያጠናክሩበት፣ የውድድር መንፈስ የሚፈጥሩበት፤ እንዲሁም በዘርፉ ተወዳዳሪ በመሆን ራሳቸውንና አገራቸውን የሚጠቅሙበት ከመሆኑ አንፃር የስፖርቱ ፋይዳ የላቀ መሆኑም አቶ ጥላሁን ከሰጡት ማበራሪያ መካከል ይጠቀሳል፡፡

ዘንድሮም በኢትዮጵያ ዳርት ፌደሬሽን አማካኝነት የተዘጋጀው 13^ኛው^ አመታዊ የዳርት ሻምፒዮና ከግንቦት 05 ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ ተካሂዷል። እንደ ፌዴሬሽኑ ፕሬዘዳንት አቶ ተስፋዬ ጎይቴ ገለፃ ከየክልሎችና ከተማ መስተዳደሮች የተውጣጡ ተወዳዳሪ ስፖርተኞች በሁለቱም ፆታዎች የተሳተፉበት አገር አቀፍ ሻምፒዮና እዚህ አዲስ አበባ (በ"የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ" ዘመናዊ ጂምናዚየም ውስጥ) የተካሄደ ሲሆን፤ ለውድድሩ ልዩ ትኩረት በመስጠት የተለያዩ አቢይና ንኡስ ኮሚቴዎች ተቋቁመው ሀላፊነታቸውን በመወጣታቸውም ውድድሩ ውጤታማ ሆኖ ሊጠናቀቅ ችሏል።

በፌደሬሽኑ ኮሚዩኒኬሽን ዘርፍ አማካይነት ይፋ ከሆነው መረጃ መረዳት እንደተቻለው፣ በዚህ ሻምፒዮና ተሳታፊ ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች በአዋቂና በታዳጊ፣ በወንድና በሴት ቡድኖች ተከፋፍለው በምድብ (ካቴጎሪ) ተወዳድረዋል። በአዋቂ ወንዶችና ሴቶች ተወዳዳሪዎች ምድብ የወንድ ነጠላ ውድድር፣ የሴት ነጠላ ውድድር፣ የወንድና ሴት የድብልቅ ውድድር፣ የወንዶች ጥንድ ውድድር፣ የሴቶች ጥንድ ውድድር፣ የወንዶች የቡድን ውድድርን እና የሴቶቸ የቡድን ውድድርን ያካተተ ሲሆን፤ በታዳጊ ወጣቶች፣ ወንዶችና ሴቶች ተወዳዳሪዎች ካቴጎሪ የታዳጊ ሴት ነጠላ ውድድር፣ የታዳጊ ወንድ ነጠላ ውድድር እና የታዳጊ ወንድና ሴት የድብልቅ ውድድሮች ተካሂደዋል።

የውድድሩን መጠናቀቅ ተከትሎም ለአሸናፊዎችና ተሳታፊዎች እንደየምድባቸው፣ ተሳትፏቸውና ደረጃቸው ከምስክር ወረቀት እስከ ዋንጫ ድረስ ሽልማት ተሰጥቷል። በዚሁ መሰረትም የስፖርት የፀባይን ከአጠቃላይ አሸናፊነት ጋር በማጣመር ትግራይ ክልል ሁለት ዋንጫዎችን የወሰደ ሲሆን፤ ከሴቶች የአዋቂ ምድብም አዲስ አበባ የአሸናፊነት ዋንጫውን ወስዷል።

በዚህ አገር አቀፍ ሻምፒዮና ላይ ለመሳተፍ ከተለያዩ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተወከሉ ስፖርተኞች የተገኙ ቢሆንም በተለያቱ ምክንያቶች ያልተገኙ መኖራቸውም ታውቋል። በመሆኑም *እነዚህ በተለያዩ ምክንያቶች በውድድሩ መሳተፍ ያልቻሉና ያልተገኙ የክልል ፌዴሬሽኖች እና ማህበራት ያሉባቸው ችግሮች ተቀርፈውላቸው በሚቀጥለው አመት የውድድሩ ተሳታፊ እንደሚሆኑ አምናለሁ* ያሉት አቶ ተስፋዬ ከዘንድሮው ሻምፒዮናም የሚቀጥለው የበለጠ ፉክክር የሚታይበት የውድድር ሳምንት እንደሚሆንም አመልክተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዳርት ፌደሬሽን እ.ኤ.አ ከጥቅምት 2017 ጀምሮ የአለም አቀፍ ዳርት ፌደሬሽን (WDF) አባል መሆኑን ተከትሎ በያዝነው የፈረንጆች አመት በጃፓን በሚካሄደው አለም አቀፍ ውድድር ኢትዮጵያ የመሳተፍ እድሉን አግኝታለች። ይህንን አለም አቀፍ ውድድር በድል ይወጣሉ ተብለው የሚጠበቁ ተወዳዳሪዎችም በዚህ የሻምፒዮና ውድድር ላይ አሸናፊ የሆኑት ሊሆኑ (ምርጫው ገና ቢሆንም) ማቻላቸው፤ አገርን ወክለው በመሳተፍ ሰንደቅ አላማችንን ከፍ አድርገው ያውለበልባሉ ተብሎ መጠበቁም የዘንድሮውን ሻምፒዮና እና ተሳታፊዎቹን ለየት አድርጎት ሰንብቷል።

የፌደሬሽኑ ፕሬዘዳንት አቶ ተስፋዬና የፅ/ቤቱ ሀላፊ አቶ ጥላሁን ውድድሩ በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁን የገለፁ ሲሆን፤ ለአጠቃላይ ዝግጅቱ መሳካትም የተባበሩትን አካላት ሁሉ አመስግነዋል። የዚህ ፅሁፍ አቅራቢም አሸናፊዎቹን “እንኳን ደስ አላችሁ!!” ይላል።